- መጠጣት፣ መመገብ፣ ጫት መቃም፣ ማስቲካ ማኘክ፣ መተኛት፤
- የዳኛ ፈቃድ ሳይኖር ጠበቃ ተጠርጣሪውን ወይም ተከሳሹን ማነጋገር፣
- የጦር መሳሪያ፣ ዱላ ወይም ስለታማ የሆኑ መሳሪያዎችን መያዝ ሆኖም የችሎቱን ስነ ስርዓት አስከባሪ፣ ተጠርጣሪውን ወይም ታሳሪውን ይዞ ወደ ችሎቱ የመጣውን ፖሊስ ወይም በልዩ ችግር ምርኩዝ ዱላ ይዞ የሚንቀሳቀስን አይጨምርም፤
- ስልጣን ካለው አካል ፍቃድ ሳኖረው በሞባይል፣ በካሜራ ወይም በቪዲዮ ፎቶ ማንሳት ወይም ድምጽ መቅዳት፣
- እንደ ሻንጣ፣ ፌስታል እና ትላልቅ ቦርሳዎች ወይም ለችሎቱ ስነ-ስርዓት የማይመች ድምጽ መፍጠር የሚችሉ ማንኛውንም እቃዎች ይዞ ወደ ችሎቱ መግባት፣
- በማንኛውም መልኩ የችሎቱን ሰላምና ፀጥታ ማወክ፤

ችሎት ፊት ስለመቆም

- በችሎት ሂደት ፍርድ ቅጣት ውሳኔ ብይን የክስ እና መልስ ቅብብል ሲደርግ፣ ክርክር ሲካሄድ፣ ባለጉዳዩ ምስክሮችን ሲያሰማ፣ አቤቱታ ሲያቀርብ፣ ትዕዛዝ ሲሰጥ፣ ውሳኔ ሲነበብ ወይም ዳኛው በያዘው ጉዳይ በሚያስችልበት ወቅት የሚመለከተው ባለጉዳይ ቆሞ መከታተል አለበት። ይሁን እንጂ ችሎቱ እንደየሁኔታው ክርክሩ የሚራዘም ከሆነ አንደኛው ወገን ሲናገር ሌላኛው ወገን እስከዚያ ድረስ እንዲቀመጥ፣ በጋራ ከተከሰሱት ወይም ከከሰሱት ሰዎች መካከል ምስክር ከሚያሰማ ወይም ከሚሰማበት ውጪ ያለው ተከሳሽ ወይም ከሳሽ እንዲቀመጥ እንዲሁም በህመም ወይም እርግዝና ወይም በአካል ጉዳት ምክንያት መቆም የማይችል ሰው እንዲቀመጥ ዳኛው ሊፈቅድ ይችላል።

<u>አድራሻ፡-</u>

ስልክ፡- +251118694441
+251118291238
+251118291250
ፖ.ሳ.ቁ. 8389
ኢ- ሜል፡-court@ffic.gov.et
ፌስ ቡክ፡-FEDERAL FIRST INSTANCE COURT OF ETHIOPIA
Or
@FFICNew2012
ዌይብ ሳይት፡- www.ffic.gov.et
ቲዊተር፡- @instantcourt
ቴሌ ግራም፡- የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት

ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት
Federal First Instance Court

ወደ ፍርድ ቤት ሲመጡ ከባለጉዳይ የሚጠበቁ ነገሮች

የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በየዕለቱ በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ደንበኞችን ሲያስተናግዱ ይውላሉ። እነዚህ ደንበኞች ወደ ፍርድ ቤት ሲመጡ ሊያዘጋጅዋቸውና ሊያደርጓቸው የሚገባቸው ነገሮችን እና ማድረግ የሌለባቸውን ነገሮች ለይተው ሊያቁ ይገባል።

ባለጉዳዮች ሊያዘጋጅዋቸውና ሊያደርጓቸው የሚገባቸው ነገሮች፡-

- በቀጠሮው ቀን፣ ቦታና ሰዓት መገኘት አለበት፤
- በቀጠሮ ቀን ለክርክሩ በአግባቡ ተዘጋጅቶ መቅረብ አለበት፣
- ዳኞች በችሎቱ ሲኖሩም ሆነ በማይኖሩበት ጊዜ በችሎቱ ክፍል ወይም አዳራሽ ውስጥ የችሎቱን ስነ-ምግባር ለማስጠበቅ በችሎቱ የሚሰጠውን የማስከበሪያ ትዕዛዝ ማክበር አለበት፤
- በችሎቱ ላይ ተራቸውን በመጠበቅ ክርክር ማቅረብ አለባቸው፤
- የፍርድ ቤቱ ባለጉዳዮች የሚጠይቁትን ዳኝነት በህጉ አግባብ የፍርድ ቤቱን ሂደት እና አሰራር በማክበር መፈጸም ይኖርባቸዋል፤
- በችሎቱ ዳኛ ክስ እየተነበበ፣ ቅጣት፣ ውሳኔ፣ ብይን ወይም ፍርድ እየተነበበ ወይም ምስክር እየተሰማ ሳለ ማንኛውም ሰው ችሎት አቋርጦ መውጣት የለበትም፤
- ያቀረቡትን ክርክር፣ ተቃውሞ እና ሃሳብ በሙሉ በቀጥታ ወደ ፍ/ቤት በአግባቡ ማቅረብ፤
- ማንኛውም ባለጉዳይ ክርክሩን ወይም ጉዳዩን ለዳኛ ሲያቀርብ ዳኛን ፊት ለፊት እየተመለከተ መሆን አለበት፤
- በችሎቱ ላይ የተነገሩት ጉዳዮች ትክክል መሆናቸው ወይም አለመሆናቸው በአይን ምልክት፣ በቅንድብ፣ በፊት ወይም በሌሎች አካል እንቅስቃሴ በመግለጽ ወይም ከዳኛው ወይም ከችሎት ዞር በማለት መናገር ከዳኛ ጋር መሟገት ክልክል ነው፤
- በችሎቱ ላይ ተቃውሞውን፣ ክርክሩን እና ሁሉንም ሃሳብ ፍትህን፣ እውነታ እና አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች ብቻ መሰረት በማድረግ ይግባኝ ማቅረብ፤
- በችሎቱ ክርክር ላይ የዳኛውን ስም መጥራት ሳያስፈልግ እንደ “ክቡር ፍ/ቤት” ወይም “ክቡር ዳኛ” ወይም ” ክብርት ዳኛ” በማለት መጥራት፤
- የችሎቱን ስነ-ምግባር የማረጋገጥ ግዴታ በቀደምትነት የዳኛው ድርሻ ቢሆንም የችሎቱ ስነ-ስርዓት እንዳይጣስ የድርሻውን መወጣት፤

ከችሎቱ ውጪና በችሎት አካባቢ የተከለከሉ ድርጊቶች

ማንኛውም ሰው በችሎቱ ላይ የሚከተሉትን ድርጊቶች መፈጸም ክልክል ነው።

- ለችሎቱ ስራ ሳያስፈልግ ማንሾካሾክ ወይም ድምጽ ከፍ በማድረግ መናገር ወይም መንጫጫት ወይም ጎኑ ካለው ወይም ከሌላ ሰው ጋር ማውራት ወይም መነጋገር፤
- በሞባይል መነጋገር፤
- ጋዜጣ እና ማንኛውንም ሌሎች ጽሁፎችን ማንበብ፤
- ሲጋራ ማጨስ፣ ቃጠሎ የሚፈጥሩ መሳሪያዎችን ይዞ መግባት፤
- በድምጽ፣ በምልክት ወይም በማንኛውም ሁኔታ ችሎቱን ማወክ ወይም ለክርክሩ አስፈላጊ ያልሆነውን ድርጊት ወይም ንግግር ማድረግ፣ የሰውን ስሜት የሚስብ/የሚነካ ተግባር መፈፀም፤